የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን

# ብሔራዊ የጎርፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ

## መፅሄት ቁጥር-2 ጥር 2016 ዓ.ም.



*በጋ 2016 ዓ.ም በሶማሌ ክልል ዶሎ ወረዳ የደረሰ የጎርፍ ክስተት*

### መግቢያ

ይህ የብሔራዊ የጎርፍ ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ቁጥር 2 መጪውን የበልግ ወቅት ማለትም ከመጋቢት እስከ ግንቦት መጨረሻ 2016 ዓ.ም ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ይሆናል፡፡ ይህ የጎርፍ ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ የተዘጋጀዉ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በሰጠው የበልግ ወቅት ትንበያ ሲሆን በበልግ ወቅት ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያው ያካተታቸው ለጐርፍ ተጋላጭ የሆኑትን ቦታዎች በመለየት ነዉ፡፡ የዚህ የጐርፍ ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ አላማ ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ፣ አደጋው ቢደርስ ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስችል ዝግጁነት እንዲኖር እንዲሁም ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ከወዲሁ የተመቻቸ ለማድረግ ነው፡፡ የብሔራዊ የጎርፍ ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ አስፈላጊ ሲሆን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በሚሰጠው ወርሃዊ ትንበያ መሰረት እና መሬት ላይ ባለው ወቅታዊ ሁኔታ የሚከለስ ይሆናል፡፡

የሀገሪቱ የረዥም ጊዜ መረጃ እንደሚያሳየው የበልግ ወቅት ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት አብዛኛው ሶማሌ፣ የደቡብ ኦሮሚያ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ክፍል፣ እንዲሁም የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ የመካከለኛውና የምስራቅ ኦሮሚያ፣ የምስራቅ አማራ፣ የደቡብና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ፣ አፋር፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ድሬ ዳዋ እና ሀረሪ ክልሎች ላይ በአንዳንድ አመታት የሚስተዋል የጎርፍ ክስተት ሊያስከትል የሚችል ከፍተኛ የዝናብ መጠን ይስተዋላል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት

አካባቢዎች በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለዘንድሮ በልግ ወቅት 2016 እ.ኢ.አ የአየር ጠባይ አዝማሚያ ትንበያ በተሰጠዉ መሰረት ከመደበኛ በላይ ያመዘነ ዝናብ እንደሚያገኙ ተጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም በተለይም በዋቢሸበሌ፣ በኦሞ ጊቤ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች የታችኛው ክፍል ላይ ያለፈው በጋ ዝናብ ከፍተኛ ጎርፍ ማስከተሉ ይታወሳል፡፡ በቀጣይ የእነዚህ የተፋሰሶች ክፍል የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ እንደመሆናቸው የተሰጠው የበልግ 2016 ወቅት መደበኛና ከመደበኛ በላይ ያመዘነ ዝናብ እንደሚኖራቸዉ ያሳያል፡፡

## ከኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለ2024 እ.ኤ.አ በልግ ወቅት የተሰጠ ትንበያ

በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስትቲዩት ከተሰጠዉ የበልግ ወቅት የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ትንበያ መረዳት እንደተቻለዉ በአብዛኛዉ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት እና የክረምት ዝናብ ቀድሞ በሚጀምርባቸው የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ጭምር መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በዚህ መሰረት ከዚህ በታች ከኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የተሰጠ ትንበያ በካርታው ላይ ለእነዚህ አካባቢዎች ከፍ ያለ ግምት ያሳያል፡፡

*Rainfall Probabilistic forecast for Belg 2024*




<u>ማስታወሻ</u>፡ ከኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለዘንድሮው በልግ ወቅት ተመሳሳይ ወቅቶች (Analog year) ተብለው የተመረጡ አመታት እ.ኤ.አ 2010 በዋናነት ሲሆን 1998 እና 2016 ተመሳሳይ አመታት ተብለው ተመርጠዋል፡፡

- የNeutral-IOD and ENSO- El Niño የውቅያኖስ ክፍል ላይ መስተዋል በበልግ 2024 እ.ኤ.አ በሀገሪቱ ደቡብና ደቡብ ምስራቃዊ ክፍል ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የመከሰት እድሉን ከፍተኛ ያደርገዋል፣

- በመሆኑም ደቡባዊ ሶማሌ፣ ደቡባዊ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ከፍ ያለ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የማግኘት ዕድል ተሰጥቷቸዋል፣
- በተጨማሪም በተደጋጋሚ የከባድ ዝናብ ክስተት እንደሚኖርና ይህንን ተከትሎ ቅፅፈታዊ ጎርፍ በከተሞች እና በጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ሊከሰት እንደሚችል፤
- በተመሳሳይ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ የመካከለኛው እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚጠበቅ ሲሆን የሰሜን ምዕራብ የአገሪቱ ክፍል ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ፤
- በአጠቃላይ ወቅታዊ እና ከተተነበዩ የአየር ንብረት ሁኔታዎች ላይ በመነሳት በልግ 2024 እ.ኤ.አ ከመደበኛ በላይ ያመዘነ ዝናብ በበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቅ መሆኑን፣
- የበልግ 2024 ወቅት ዝናብ አጀማመር ቀደም እንደሚልና አወጣጡም እንደሚዘገይ፣
- እየታየ ያለው Neutral-IOD and ENSO- El Niño የውቅያኖስ ክፍል ለሰሜናዊ አጋማሽ ኢትዮጵያ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ለሆነ ዝናብ አስተዋፆ እንደሚያደርግ፣
- ከመደበኛ በላይ እና ወደ መደበኛ የተጠጋ የአየር ሙቀት በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍል ላይ እንደሚኖር ተጠቁሟል፡፡

## የጐርፍ አደጋ ስጋት ሊኖርባቸዉ ይችላል ተብለዉ የተለዩ ቦታዎች

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የ2016 ዓ.ም የበልግ ወቅት አየር ሁኔታ ትንበያን እና ለወቅቱ የተሰጠውን ተመሳሳይ አመታትን መሰረት በማድረግ በ2016 ዓ.ም በልግ ወቅት የጎርፍ አደጋ ስጋት ያለባቸውን አካባቢዎች በየክልሉ በመለየት ዝርዝሩ እንደሚከተለዉ ተሰርቷል፡፡ ከታች የተጠቀሱት ወረዳዎች በዋና ዋና ወንዞች የታችኛው የተፋሰስ ክፍል የሚገኙና በአነስተኛ እና በዋ ዋና ወንዞች ሙላት ይበልጥ ስጋት ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪም በአገሪቱ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ የሚጠበቀው ከመደበኛ በላይ ያመዘነ ዝናብ ለቅፅበታዊ ጎርፍ አደጋ ሊጋለጡ ስለሚችሉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ወረዳዎች ላይ የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች አስፈላጊ መሆኑን ለመጠቆም ነው፡፡

### ሰንጠረዥ 1፡ የጎርፍ ተጋላጭ ወረዳዎች በክልልና ዞን

| ክልል | ዞን | ወረዳ |
|---|---|---|
| ሶማሌ | አፍዴር | ምዕራብ ኢሚ፣ ጨረቲ፣ ዶሎባይ፣ ጎድጎድ፣ ኮለሌ፣ ራሶ፣ ሀረገሌ፣ አፍዴር፣ ባሬይ እና ኤለክሪ |
| | ሊበን | ዶሎ ኦዶ፣ ቦኮልማዮ፣ ጉራደዳሞሌ፣ ጎሮቦቀቅሳ እና ፊልቱ |
| | ዶሎ | ዋርዴር፣ ቦክህ፣ ዳኖድ፣ ላህልዩብ፣ ዳራቶሌ፣ ጋልህሙር እና ጎላዲን |
| | ቆራሄ | ቀብሪደሃር ወረዳ፣ ቀብሪደሃር ከተማ፣ ሸኮሽ፣ ደበወይን፣ ጎግሎ፣ ቦዳሌይ፣ አል ኦጋዴን፣ ሂግሎላይ እና ሸላቦ |
| | ኤረር | ፊቅ፣ ሳላሂድ፣ ሀመሮ፣ ለገሂዳ እና መዩሙልቂ |
| | ዳዋ | ሞያሌ፣ ሁደት፣ ጋዳዱሞ እና ሙባረክ |
| | ጀረር | ደጋሃቡር፣ ጉናጋዶ፣ ጋሻሞ፣ ቢርቆድ፣ አዋሬ እና ደገሀመዶ |
| | ነጎብ | ሳገግ፣ ጋርቦ፣ ዲሁን፣ ኤልዋዬ፣ አዩን፣ ሃራሬ እና ሆርሻጎህ |
| | ፋፈን | ባብሌ፣ ቀበሪበያህ፣ ቀበሪበያህ ከተማ፣ ሃርሸን፣ ጎልጃኖ እና ጂግጂጋ ከተማ |
| | ሸበሌ | ቀላፎ፣ ምስራቅ ኢሚ፣ ሙስታሂል፣ አዳድሌ፣ ደናን፣ በራኖ፣ ፌርፌር፣ ኢላሌ፣ አባ ኮሮው፣ ጎዴ ከተማ እና ጎዴ |

| | | |
|---|---|---|
| **ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል** | ጎፋ | ኡባደብረፀሀይ፣ ዛላ፣ ዳራሞሌ እና ቁጫ |
| | ወላይታ | ሶዶ ዙሪያ፣ ሁምቦ፣ ዳሞት ወይዴ እና ቦረዳ |
| | ጋሞ | አርባምንጭ ዙሪያ፣ ቦንኬ፣ ከንባ እና ምእራብ አባያ |
| | ጌድኦ | ወናጎ፣ ይርጋጨፌ እና ገደብ |
| | ኮንሶ ዙሪያ | ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ አማሮ እና ደራሼ ልዩ ወረዳዎች |
| | ደቡብ ኦሞ | ኛንጋቶም፣ ዳስነች፣ ሃመር፣ በናፀማይ፣ ጅንካ ከተማ እና ሳላማንጎ |
| **ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል** | ቤንችማጂ | ማጂ፣ ሱርማ እና ጉራፈርዳ |
| | ከፋ | ደቻ እና ጨታ |
| **ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል** | ስልጤ | ስልጤ፣ ዳሎቻ፣ ላንፈሮ እና ሳንኩራ |
| | አላባ | አላባ ቁሊቶ፣ አቶቴ፣ ወይራዲጆ እና ወይራ |
| | ሀድያ | ሻሸጎ እና አንሌሞ |
| | ጉራጌ | መስቃን፣ ማረቆ እና ሶዶ |
| **ኦሮሚያ** | ቦረና | ዳስ፣ ድሬ፣ ዲሎ፣ አሬሮ፣ ሚዮ፣ ተልተሌ፣ ሜጋ ከተማ፣ ሞያሌ እና ያቤሎ |
| | ጉጂ | አዶላ፣ ኡራጋ፣ ሰባቦሩ፣ ጎሮዶላ እና ሊበን |
| | ምዕራብ ጉጂ | ገላና፣ አባያ፣ መልካ-ሶዳ፣ ዱግዳ-ዳዋ እና ቡሌ-ሆራ |
| | ባሌ | ዶሎ-መና፣ መዳ-ወላቡ፣ አጋርፋ፣ ጋሰራ፣ በርበሬ፣ ጎሮ እና ጉራ-ዳሞሌ |
| | ምስራቅ ባሌ | ጊኒር፣ ራይቱ፣ ሰዊና፣ ጎሎልቻ፣ ዳዌ-ቃቸን፣ ዳዌ-ሰረር እና ለገሂዳ |
| | አርሲ | ዶዶታ፣ ዝዋይ-ዱግዳ እና ሂጦሳ |
| | ምዕራብ አርሲ | ሲራሮ፣ ሻላ እና ሻሸመኔ ዙሪያ |
| | ምስራቅ ሸዋ | ቦሰት፣ መርቲ እና አዳማ |
| | ምዕራብ ሀረርጌ | ሃዊ-ጉዲና እና ቦኬ |
| | ምስራቅ ሀረርጌ | ባብሌ፣ ጎሎኦዳ፣ መኢሶ፣ መዩ እና ሚደጋቶላ |
| **አፋር** | ዞን 1 | ጭፍራ፣ ሚሌ እና አዳር |
| | ዞን 2 | ኩነባ፣ ዳሎል፣ በርሃሌ፣ አባላ፣ መጋሌ እና እረብቲ |
| | ዞን 3 | ዱለቻ፣ አሚባራ፣ ገዋኔ እና ቡሬሙዳይቱ |
| | ዞን 4 | ጉሊና፣ እዋ፣ ያሎ፣ ቴሩ እና አዉራ |
| **ሲዳማ** | | ሎካ አባያ፣ ቦርቻ እና ሃዋሳ ዙሪያ |
| **ሐረሪ** | | የገጠር ቆላማ ቀበሌዎች |
| **ትግራይ** | | ደቡባዊ እና ደቡብምስራቃዊ አካባቢ |
| **አማራ** | ሰሜን ወሎ | ሀብሩ፣ ጉባ ላፍቶ እና ቆቦ |
| | ደቡብ ወሎ | ተለሁደሬ እና ቃሉ |
| | የኦሮሞ ዞን | ዳዋ ጨፋ እና ዳዋ ሀረዋ |

በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ የጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች እንዲሁ የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር እና የገጠር ቀበሌዎች በጎርፍ ተጋላጭነት ተካተዋል፡፡

ካርታ: በበልግ 2016 ዓም የጎርፍ ተጋላጭ ቦታዎች አመላካች ካርታ




ለዘንድሮ በልግ 2016 ዓ.ም የተሰጠው ትንበያ በአብዛኛዎች የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የሚጠበቅ በመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት አካባዎች በተጨማሪ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚከሰተው ከባድ ዝናብ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም ዝናብ በመጠንና የዝናብ ቀናት በሚበዛባቸው አመታት የመሬት አቀማመጣቸው ገዳላ ገደል በሆኑና በተለይም በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙና አጎራባች ወረዳዎች ለመሬት መንሸራተት አደጋ ተጋላጭ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ ከወዲሁ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች፤

**ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፡-** የስምጥ ሸለቆ አጎራባች የሆኑ ወረዳዎች፣ **ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል** በክልሉ በሰሜናዊምስራቅ በኩል የሚገኙ ወረዳዎች፣ **ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል** የስምጥ ሸለቆ አጎራባች የሆኑ ወረዳዎች፣ **ኦሮሚያ ክልል** ሰሜን ሸዋ ዞን ሰሜናዊና ምዕራባዊ ወረዳዎች፣ **አማራ ክልል** የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ እንዲሁም የደቡብ ወሎ አዋሳኝ የሆኑ የሰሜን ሸዋ ወረዳዎች ናቸው፡፡

**<u>የቅድመ ዝግጅትና ጉርፍን አስቀድሞ ከመከላከል አንጻር በቅድሚያ ሊሰሩ የሚገቡ ስራዎች፡-</u>**

የጎርፍ ስጋት ያለባቸው አካባቢዎች ጎርፍ ለሚያደርሰው አሉታዊ ተፅዕኖ የሚወሰዱ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ጉዳቱን ማቅለያ ተግባራት ላይ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አጋር

ድርጅቶች የሚከተሉትን ቁልፍ መነሻ ስራዎች በስፋት እየተሰራበት ካለው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስራዎች እንደ አንድ ክፍል ተደርጎ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

- ለጎርፍ ስጋት ተጋላጭ የሆኑትን ማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ ተደራሽ ማድረግ በብሔራዊ የጎርፍ ግብረሃይልና በክልሎች ግብረሃይል መካከል ተከታታይነት ያለው መረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ፤
- በጎርፍና የመሬት መንሸራተት ስጋት ውስጥ ያሉትን አካባቢዎች በተመለከተ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ማሰራጨትን ጨምሮ የጎርፍ መከላከያ መዋቅሮችን ማጠናከር፤
- ማህብረሰቡ ላይ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ንቁ ሆኖ እንዲጠብቅ ግንዛቤ መፍጠር፣
- በደጋማ ቦታዎች እና በዝቅተኛ አካባቢዎች ባለው ማህበረሰብ መካከል ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ፤
- በተዳፋት ቦታዎች የጎርፍ ፍሰት ፍጥነትን ቀድሞ ማወቅ እንዲቻልና ለሚወሰደው እርምጃ ዝግጅት ማድረግ፤
- አደጋው ቢፈጠር በወቅቱ ወደ ከፍተኛ ቦታ ማህበረሰቡን ማንቀሳቀስና በወቅቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ማቅረብ የሚቻልበትን አሰራር ታሳቢ ማድረግ፤
- በወቅቱ ተደራሽ ለመሆን በንቃትና በቅርበት የስጋት አካባቢዎችን ክትትል ማድረግ፡
- የማስጠንቀቅያ፣ የዝግጅት ስራዎችንና አደጋውን ለማቅለል የሚወስዱ ተግባራትን እንዲሁም የወንዞችን የውሃ ከፍታ መጠን መከታተል፣ የክልሎችንና የዞኖችን የጎርፍ ግብረሃይል ድጋፍ ማድረግ፣ እንደገና ማንቀሳቀስና ማጠናከር፤
- ከታች ካለው የቀበሌ መዋቅር እስከ ላይ ያለው የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የቅንጅት ስራዎችን፣ የመረጃ ልውውጥ መንገዶችን መከታተልና ማጠናከር፤
- የዝግጅት እና የመከላከል ተግባራት ውሃ ማቆር ሥራዎችን ጭምር በማበረታታት፣ የንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፣ ውሃን ማከም፣ ንጽህናን ለመጠበቅና በሽታን ለመከላከል የሚወሰዱ ርምጃዎች ማጉልበት፣ እንደ አጣዳፊ ተውከትና ተቅማጥ የመሳሰሉትን ተላላፊ በሽታዎችን በቅርብ መከታተልና መከላከል፣ ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ የስነ-ምግብና ጤና ነክ የሆኑ ስራዎችን በመስራት በጎርፍ ምክንያት በህይወትና በንብረት ላይ የሚደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ መቀነስ፤
- የተቀናጀ ዘርፈ ብዙ ሴክቶራል የጐርፍ መጠባበቂያ እና ምላሽ እቅድ እንደ አስፈላጊነቱ ማዘጋጀት እና በተለይ ለአደጋው ምላሽ መስጠት የሚያስችል ግብ ያደረገ ስራን ማከናወን፡
- የቅፅበታዊ ጐርፍና የወንዝ ሙላት የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የጎርፍ ማፋሰሻ ግንባታ እና ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የጐርፍ መከላከያ ሥራዎችን እንዲሁም ተሳትፎና ግንዛቤን በማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት የጐርፍ መከላከያ ሥራዎችን ማጠናከር እና ሌላም አስፈላጊ የሆኑ የመከላከያ ፋሲሊቲዎችን ማሻሻል፤
- ጐርፍን ለመከላከል በሚሰሩ በሁሉም ተግባራት ውስጥ የማህብረሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ።